አንዳንድ ጥቃቶች የማይወገዱ ሲሆኑ፣ ቀላል አለመግባባቶች ወደ መክረር ወይም ግድያ እንዳይለወጡ የሚከተሉትን ጥቆማዎች ይመልከቱ።

- ወደ ኃይል የሚለወጥ የከረረ አለመግባብት ውስጥ ከሆኑ ትተው ይሂዱ። በዚህ ሁኔታ መቀጠሉ መጥፎ ውሳኔ ነው።
- በማንኛውም ጊዜ ሽጉጥ፣ ሰንጢ ወይም ህጋዊ ያልሆነ መሳሪያ አይያዙ። መሳሪያ መያዝ ሁነታዎችን ሊያባብስና እራስዎን ወይም ሌላ ንጹህ የሆነ ሰውን ሊጎዳ ይችላል።
- ከመጠን በላይ አይጠጡ፤ ወይም ይጠጡ ከነበሩ በአስተሳሰብዎ ላይ የሚያመጣውን ጉዳት አስቡ። ለብዙ ጥቃቶች መጠጥ መነሾው ነው።

ጥቃት ሲካሄድ ካዩ ውዲያውኑ ለፖሊስ ላማስታወቅ 9-1-1 ይደውሉ። ከፍተኛ ጉዳት ለማቆም የመጨረሻው ምርጫ ካልሆነ በስተቀር ግጭቱ ወስጥ ዘለው አይግቡ



## ተጭማሪ የደህንነት

በእለት የእለት ኑሮዎ ከወንጀል ለመዳን በድህረ ገጻችን www.mpdc.dc.gov/safety. የሚገኙ ተጨማሪ ሰነዶችን ይመልከቱ። ወይም ወደ አቅራቢያዎ የፖሊስ ጣቢያ ይሂዱ። በአቅራቢያዎ ያለውን ለማወቅ በድህረ ገጽ www.mpdc.dc.gov/districts ይመልከቱ።

## ተካፋይ ይሁኑ!

በተናጠል የሚሠራ ግለሰብም ሆነ ድርጅት ወን ልን ሊያቆም አይችልም። ፖሊስና ዜጋዎች በቡድን መሥራት አለባቸው። ወን ልን ለማስወገድና ሰላም ያለው አካባቢ ለመገንባት የኮሎምብያ ዲስትሪክት የአካባቢ ጥበቃ ዘዴ ሕብረተሰቡና ፖሊስ አብረው የሚሠሩበት መንገዶች አሉት። እነኝህም የአካባቢ የፖሊስ አገልግሎት ስብሰባዎች፣ የዜጋ ቃኝዎችና ሌሎችን ይጨምራል። በበለጠ ለማወቅ ለአካባቢዎ የፖሊስ ዲስትሪክት ይደውሉ።

1ኛ ዲስትሪክት ዋና፡ ... (202) 698-0555 ......TTY: 727-8506
ቅርንጫፍ:... (202) 698-0068 ......TTY: 543-2352
2ኛ ዲስትሪክት ዋና፡...... ... (202) 715-7300 ......TTY: 364-3961
3ኛ ዲስትሪክት ዋና፡......( (202) 673-6815 ......TTY: 518-0008
4ኛው ዲስትሪክት ዋና...... .. (202) 715-7400 ......TTY: 722-1791
ቅርንጫፍ... (202) 576-8222 ......TTY: 576-9640
5ኛው ዲስትሪክት ዋና: ... (202) 698-0150 ......TTY: 727-5437
6ኛው ዲስትሪክት ዋና.... ... (202) 698-0880 ......TTY: 398-5397
ቅርንጫፍ:... (202) 698-2088 ......TTY: 281-3945
7ኛው ዲስትሪክት ዋና..... (202) 698-1500 ......TTY: 889-3574

## ስለወን ል የሚያውቁት ነገር ከአለ በሚስጥር አይያዙት።

ለፖሊስ ሊያካፍሉት የሚፈልጉት ጠቃሚ መረጃ ካለዎት፣ ስም ያልተጠቀሰበት የወን ል ጥቆማ መስመር እና የቴክስት ጥቆማ መስመር ለአካባቢው ፖሊስ ስም ሳይሰጡ መስጠት ይችላሉ። ሰባት ቀን በሳምንት 24 ሰዓት በቀን (202) 727-9099 ይደውሉ ወይም በ50411 ቴክስት ያድርጉ። መረጃው ብቻ እንጅ ስምዎ አይገለጽም። የሚሰጡት መረጃ ገንዘብ ሊያስገኝ ይችላል። ለበለጠ መረጃ በድህረ ገጽ www.mpdc.dc.gov/tipline ይመልከቱ።

GIVE 5-0 THE 4-1-1

ለፖሊስ መረጃ አለዎት?
**(202) 727-9099 ይደውሉ**
**50411 ቴክስት ያድርጉ**

Government of the District of Columbia
Metropolitan Police Department
300 Indiana Avenue, NW
Washington, DC 20001

*April 2013*

## ለደህንነትዎ



# ከመዘረፍ እና ከመጠቃት እራስዎን መጠበቅ።

ከሌቦችና ከኪስ አውላቂዎች እራስዎንና ንብረትዎን እንዴት እንደሚከላከሉ ጥቆማዎች።

# በመንገድ ላይ እራስዎን እንዴት እንደሚከላከሉ ይወቁ።

## አጥቂ ላያጋጥምዎት ይችላል፣ ይሁን እንጅ ጥቃት ቢደርስብዎት ምን እንደሚያደርጉ ማወቅ ጠቃሚ ነው።

ዘረፋና ማጥቃት ከባድ ወንጀሎች ናቸው። ለጥቃቱ በዙ ጊዜ ዋና መንሻው ገንዘብ ሲሆን፣ ይህን ለመፈፀም በአካል ላይ የሀይል ጥቃት ስለሚጠቀሙ እንደ ወንጀል ይቆጠራል። መሰረታዊ መከላከያው ማስተዋልና ንቁ መሆን ነው።

» ከተቻለ በማታ ብቻዎን አይሂዱ። በተቻለ መጠን በቡድን ይሂዱ። ብዙ ከመሆን ደህንነት ይገኛል።

» የት እንደሚሄዱ፣ የሚደርሱበትን ወይም የሚመለሱበትን ሰዓት ለቤተሰብ ወይም ለጓደኛ ይንገሩ። ይህንን ካደረጉ፣ ችግር ካለ በተቻለ ፍጥነት ለፖሊስ ማስታወቅ ይቻላል።

» የተቻለውን ያህል መብራት ባለው አካባቢ ይሁኑ። ጠባብ መንገዶችን፣ ባዶ ቦታዎችን፣ ዛፎች የበዙባቸው አካባቢዎችን ወይም ሌሎች ገለልተኛ ቦታዎችን አስወግዱ። እነኝህ ቦታዎች ብዙ ብርሀን ወይም መንገደኛ የለባቸውም።

» በተቻለ መጠን በእግረኛ መንገድ ይራመዱ። በጠርዙ አካባቢ ይራመዱ፣ ችፍግ ያለና መደበቂያ ያለበት አካባቢ አይሂዱ።

» በአስፋልት መንገድ የሚሄዱ ከሆነ በትራፊኩ (መኪናዎቹ) ተቃራኒ ይሂዱ። ከሚከናው ጎን ለጎን የሚሄድ በተቃራኒ ከሚሄድ ሰው ይልቅ በቀላሉ ለመከተልና አስገድዶ መኪና ውስጥ ለማስገባት ይቻላል።

» በእርግጠኝነት፣ ፊትለፊት እና ሳያመነቱ ይራመዱ። ከማያውቋቸው ሰዎች ጋር ለመነጋገር አይሞክሩ።

» በቀላሉ ለመንቀሳቀስ የሚያስችሉ ልብስና ጫማ ይልበሱ። ብዙ ዕቃዎች አይያዙ።

» ሁልጊዜ አካባቢዎችዎን ይመልከቱ።

» የጆሮ ማዳመጫ (ሄድፎን) ካደረጉ የአካባቢዎን ድምጽ ለመስማት እንዲችሉ ድምፁን ዝቅ ያድርጉ።

» በማያውቁት ሰው መኪና አይሂዱ።

» ማንኛውንም አጠራጣሪ ድርጊት ወይም ሰው ለአካባቢው ፖሊስ መሥሪያ ቤት 3-1-1 በመደወል አስታውቁ። አጣዳፊ ከሆነ 9-1-1 ይደውሉ።

» በጣም ብዙ ጥሬ ገንዘብ፣ ውድ የሆኑ ጌጣጌጦችንና የመሳሰሉትን ሕዝብ ባለበት ቦታ አይያዙ ወይም አያሳዩ።

» ብዙ ገንዘብ መያዝ ካለብዎት በትንንሹ ከፋፍለው የተለያዩ ቦታዎች እንደ ቦርሳ፣ የጎን ኪስና በመሳሰሉት ውስጥ ይክተቱ።

### በመንገድ ላይ ማድረግ የሚገባዎ

» በማንኛውም ቦታ - መንገድ ላይ፣ በመሥሪያ ቤት ህንፃ፣ የገበያ አዳራሽ፣ አውቶቡስ ወይም ባቡር ጣቢያ - ንቁ በመሆን አካባቢዎን ይቃኙ።

» በሚሄዱበት ሁሉ እርግጠኝነት፣ የመረጋጋት መንፈስና የሚሄዱበትን እንደሚያውቁ ያሳዩ።

» ስሜትዎን እመኑ። አንድ ነገር ወይም ሰው ካስጨነቀዎት፣ ሰውዬውን ይራቁ ወይም ቦታውን ለቀው ይሂዱ።

» የሚኖሩበትንና የሚሠሩበትን አካባቢ ጠንቅቀው ይወቁ።

» በምሽት ክፍት የሚሆኑ የፖሊስ፣ የእሳት አደጋ፣ የሕዝብ ስልኮች፣ ሆስፒታሎች፣ ሬስቶራንቶችና መደብሮች ያሉበትን አካባቢ ይወቁ።

» አንድ ሰው ሊሰርቅዎት ከፈለገ ህይዎትዎን አድነው ንብረትዎን ይስጡ።

» ወንጀሉን ለፖሊስ ሪፖርት ያድርጉ። አጥቂዎን በደንብ ለመግለጽ ይሞክሩ። የእርስዎ ተገባርጊ ሌሎችን ከመጠቃት ያድናቸዋል።

» ለራስ መከላከል የሚወሰዱ እርምጃዎች እንደመከላከያ ከተጠቀሙባቸው ውጤታማ ናቸው። አደጋ ከመድረሱ በፊት የመከላከያ እርምጃዎችን እንደ መሮጥ፣ መደበቅ፣ በመጮህ ማስጠንቀቂያ መስጠትዎትን ይጠቀሙ። ብዙ ጊዜ ሰዎች ለጩኸት አፋጣኝ መልስ ይሰጣሉ።



### በመኪናዎ ውስጥ ደህንነት

» መኪናን የመስረቅ ወንጀል በሀገሩ ከዳር እስከ እዳር በዜና ይሰማል። ይሁን እንጅ፣ በስታትስቲክስ ሲመለከቱት የእርስዎ በዚህ ወንጀል የመጎዳት እድልዎ በጣም ትንሽ ነው። ጥንቃቄ መውሰድ ጉዳትን ይቀንሳል።

» መኪናዎን በመሳሪያ በኃይል ሊዎስድብዎት ካስፈራራዎት፣ መኪናዎን ይስጡት!

» አይከራከሩ። ህይዎትዎ ከመኪናዎ የበለጠ ዋጋ አለው!

» ከአካባቢው በተቻለ ፍጥነት ይልቀቁ።

» መኪናዎን በኃይል ሊዎስድብዎት የሞከረው ሰው ምን እንደሚመስል፣ ፆታው፣ ዘሩ፣ ዕድሜው፣ የዓይኖቹ ቀለሞች፣ ልዩ ምልክቶችና ልብሱን ለማስታወስ ይሞክሩ ።

### የገንዘብ ማውጫ ማሽን ላይ የሚወሰድ ጥንቃቄ

» የሚያውቁትን የገንዘብ ማውጫ ማሽን ለመጠቀም ይሞክሩ። በየቦታው ከሚገኙ ማሽኖች ይልቅ በባንክ ቤቶች አካባቢ የሚገኙትን ማሽኖች ይጠቀሙ።

» አካባቢዎን ጠንቅቀው ይመልከቱ። ገንዘብ ከማውጣትዎ በፊት አካባቢውን ይመልከቱ።

» አጠራጣሪ ሰው ወይም ነገር ካዩ ገንዘብ ማውጣቱን ትተው ወደ ሌላ የገንዘብ ማውጫ ማሽን ይሂዱ።

» ከመሸ በኋላ ገንዘብ ማውጣት ካለብዎት ደህና መብራት መኖሩን ያረጋግጡ።

» ከገንዘብ ማውጫ ማሽን ያወጡትን ገንዘብ በእጅዎ ይዘው አይሂዱ። መቁጠር ካለብዎት እዛው ሆነው ይቁጠሩ።

» መኪናዎ ውስጥ ሆነው ከገንዘብ ማውጫ ማሽን ገንዘብ ሲያወጡ አካባቢዎን ይመልከቱ እንዲሁም የመኪናዎን በር ይቆልፉ።

### ጥቃቶችን መከላከል

» ጥቃቶች በመሰረቱ በመሳሪያ ወይም አለመሳሪያ የሚካሄዱ ሲሆኑ፣ በቤት ውስጥ፣ በሕዝባዊ ቦታ፣ በማይተዋወቁ ሰዎች፣ በጓደኛሞች፣ በሚተዋወቁ ወይም በሚዋደዱ ሰዎች መካከል የሚደረጉ ድብድቦች ናቸው።

» በጣም ከባድ የሆኑት ጥቃቶች የሚፈፀሙት በመሳሪያ ወይም ዓላማው ለመግደል ሲሆን ነው።

በጣም ከባድ ያልሆኑት ጥቃቶች "ቀላል ጥቃቶች" ይባላሉ። አብዛኛውን ጊዜ ቀላል ጥቃቶች የተነሳበት አለመግባብት ወዲያውኑ መፍትሄ ካላገኝ ወደ ከባድ ጥቃቶች ወይም ግድያ ሊለወጡ ይችላሉ።